PANORAMA # XXXII

**የትዝብት አድማስ**

**ሐምሌ 4 ቀን 2000**

## ***<u>የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!</u>***

# ***<u>ከውስጥ አርበኞች ጠንቀቅ</u>***

***የአንድ ሀገር ሕዝብ፥ በታሪኩ ሂደት፥ መንታ መንገድ ላይ ከደረሰ፥ ሌላ ሦስተኛ አማራጭና መፈናፈኛ ሊኖረው ይቸግረዋል። እበላ ባዩና ባንዳው ግን ምን ጊዜም ቢሆን የቆመው ለራሱ ኑሮ ብቻ በመሆኑ፥ ሌሎች አማራጮች አያጣም። ለግል ጥቅሙ ማሳኪያ እስከሆኑለት ድረስ ሰብዕናውን ሽጦም ቢሆን ከሕዝብ ጠላቶች ጋር ተባብሮ ሀገር ከመጉዳት ወደ ኋላ አይልም። ይህ በጣሊያን ወረራና በዘመነ ደርግ የተረጋገጠ ነው። በአንድ ሀገር የመንታ መንገድ ክስተት ግን አንደኛውን ወይም ሌላኛውን በግድ ለመምረጥ የሚፋጠጥበት ጊዜ ይመጣል። ከሁለቱ አንደኛውን ሳይመርጥ፥ ማህል ሰፋሪና ነገር አምታች እየሆኑ መቀጠል ከማይደረሰበት ወቅት መምጣቱ አይቀርም። ዛሬ ማን ከማን ተለይቶ ታውቋል። ወያኔን አምርሮ የሚቃወመውና እያስመሰለ የሚፏክተው ተለይቷል። የኢትዮጵያን ቆዳ በመልበስ ኢትዮጵያዊ መስሎ መታየትና ኢትዮጵያዊ ሆኖ ለኢትዮጵያ ሕዝብ መሰዋት የተለየ ነው። ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅምና ለሀገራቸው ክብር የተሰውት፥ ወይም እንበለ ፍርድ በየማጎሪያው ለዓመታት የሚሰቃዩት፥ ወይም ደግሞ ለያዙት ሕዝባዊ ዓላማ ሲታገሉ መዳረሻቸው ያልታወቀው ዜጎችና በአፍ ብቻ ከሕዝብ ወገን እንደቆሙ አስመስለው በተግባር ግን ከሕዝብ ጠላት ከመለስ ዜናዊ ጋር የወገኑት እኩል ሊሆኑ አይችሉም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ ማን ምን መሆኑን በማያሻማ መንገድ ከአረጋገጠበት ወቅት ላይ ነው ያለው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ወዳጅ ጠላቱን በሚገባ ማወቁ፥ በትግሉ ላይ የሚያመጣው አንደምታ እጅግ ከፍተኛ እንደሚሆን መታወቅ አለበት። ይህም 1997ቱ ግንቦት ወር ባደረገው አርዕድ አንቀጥቅጥ የተቃውሞ ሰልፍ ታይቷል። በዚሁ ወር በተደረገውም የወያኔ ምርጫ ድምፁን ለማን እንደሰጠ በማያሻማ መንገድ አረጋግጧል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ወያኔን፥ አልፈልግህምና ከሥልጣን መውረድ አለብህ ብሎ መወሰኑን በከፍተኛና በአንድ ድምፅ አሳውቋል። ይህንንም ውሳኔውን ከወያኔ የበላይ ጠባቂዎች በስተቀር መላው ዓለም በሚገባ ተረድቶታል። አራት ነጥብ!***

***ወቅቱ፥ ወለም ዘለም ለማለት የሚያመች ሆኖ አልተገኘም። ሁኔታዎቹ እንደ ቀትር ፀሐይ ግልፅ ሆነዋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ድምፅ፥ በመለስና ግብረ-***

አበሮቹ ተሰርቋል፡ ድምጼ መሰረቅ የለበትም ብሎ በመቃወሙ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአደባባይ ተረሸኗል። በርካታ ዜጎች አይቀጡ ቅጣት ደርሶባቸዋል። ብዙዎቹ ወኀኒ ወርደዋል። የሕዝብን ቁጣ አስተነፍሳለሁ ብሎ በማመኑም በሀገሪቱ ላይ የአስቸኳይ አዋጅ አውጆም ነበር። ምርጫውንም እኔ አቸንፌያለሁ ብሎ  አስታውቋል። የኢትዮጵያ ሕዝብም ከፍተኛ መስዋዕትን ለሚጠይቀው ትግል ቆርጦ ተነስቷል።  መለስ ዜናዊ በበኩሉ፥ ለተቃዋሚዎቹ ሦስት ምርጫዎች ሰጥቷቸው ነበር፥ በወቅቱ። ይኸውም፦

ሀ) ማሸነፌን ተቀብላችሁ በፓርላማ ውስጥ በመግባት አንገት ደፍታችሁ ተገዙ፤ (ይህንን ምርጫ የተቀበሉ ጉደኞች አሁንም ለወያኔ በመገዛት ላይ ናቸው። የሕዝቡን አደራ በመብላት ማለት ነው!)

ለ) አይ፥ በፓርለማ ገብቶ መሥራት አይቻልም ካላችሁ ደግሞ፥ ልክ እኔ ከደርግ ጋር አብሮ መስራት አይቻልም ብየ ጫካ በመግባት እንደተዋጋሁት ሁሉ፥ ያህንኑ ምርጫ ወስዳችሁ መዋጋትና እኔን በጦር ኃይል ገልብጣችሁ ሥልጣን መያዝ፥ የእናንተ ጉዳይ ነው፤

ሐ) ይህ ሳይሆን ቀርቶ፥ የኔን "ሕገ-መንግሥት" በመቃወም ካስቸገራችሁ ግን፥ ወኅኒ  ነው የማወርዳችሁ፤

በማለት በማያሻማ ቋንቋ ተናግሮ ነበር።

በወቅቱ የነበረው የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሀቅ ይህ ነበር። አሁንም ያው ነው።  በሂደት ግን የኃይሎች አሰላለፍና ጎራው ግልፅ ሆኖ ተቀምጧል።  በዚህ ሁኔታ፥ የፖለቲካ ተቃዋሚ ድርጅቶች እንደ ገና ዳቦ በሁለት ዓይነት እሳት ውስጥ እንደሚገኙ ይታያል። ከላይ የወያኔ ፍህምና ረመጥ፥ ከታች ደግሞ የሕዝቡ ነዲድ ማለት ነው። በሁለት እሳቶች ውስጥ እየተርመጠመጡ መሄድና መቆየት አይቻልም። ሕዝቡ እያላቸው ያለው፥ ድምጼን የሰረቀውን ወንበዴ ወያኔን አስወግዳችሁ መንግሥት መስርቱና ከወያኔ አገዛዝ አላቅቁኝ ነው። የመለስ ድጋፍ ሰጭ ቡድኖች እንድትሆኑ ሳይሆን፥ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ለመመስረት የሚያስችላችሁን ኃይል አግኝታችሁ ሀገራችንን ከዘረኛ ሥርዓት ነፃ አውጧትና ወደ ልማትና ዕድገት ጎዳና አተኩሩ ነው። ይህን የሕዝብ መሠረታዊ ጥያቄና ጩኸት መመለስ፥ ለሕዝብ እታገላለሁ የሚል የማነኛውም የተቃዋሚ ድርጅት ዓይነተኛ ዓላማና ማዕከላዊ ተግባር በሆነ ነበር። ይህንን መሠረታዊ ግዴታ ሳያሚሉ፥ አንድን እግር ከወያኔ ጋር ማቆራኘት፥ ሌላውን እግር ከሕዝብ ጎራ ማድረግ አይቻልም።  ይህንን ለማድረግ መሞከር ትርፉ ተገነጣጥሎ መቅረት ይሆናል። ኅሊና ያለው ሰው ቅድሚያ መስጠት ያለበት፥ በታሪክና በትውልድ ዘንድ ተጠያቂ የሚያደርገውን ተግባር እንዳያደርግ መጠንቀቁ ላይ ነበር፥ አሁንም ያው  ነው።

ከስትራተጂያዊ ወይም ከዘላቂ ራዕይ አኳያ ሲታይ፥ በሀገራችን የዴሞክራሲያዊ (ዴሞክራታይዜሽን) ሂደት ከፍተኛውን ቦታ መያዝ

እንደሚገባው ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ይቀበለዋል ተብሎ ይገመታል፡፡ ይህ ከሆነ ዘንድ፥ በሚቀጥለው የወያኔ ምርጫ ለመሳተፍና የዘረኞችን አገዛዝ ቅብዓ ሜሮን እየቀቡ፥ "መልከ-ጥፉን በስም እየካሱ" ለወያኔ ሽርጉድ ማለት ሀገሪቱንና ዜጎቿን ይጎዳል እንጅ የሚያመጣው ፋይዳ የለውም፡፡ ለዴሞክራታይዜሽን ሂደት ምንም የሚያበረክተው አስተዋጽዖም አይኖረውም፡፡ የወያኔ የምርጫ ተዋናይ ለመሆን ወደዚያ ጉዞን ማስተካከል ምንም የሚያመጣው ፋይዳ የለውም፡፡ ጉዳት ግን አለው፡፡ በሚቀጥለው የወያኔ ፓርላማ ምርጫ ከአሁኑ ለመዘጋጀት የሚደረገው የጋራ ግንባርና ትብብር፥ ጎራው እየለየ፥ ሰልፉ እየታየ መምጣቱ ግን ሁሉንም ሂደት ፍንትዉ አድርጎ ለማሳየት ይረዳል፡፡ ይህ ክስተት በሕዝቡ ትግል ቀዝቃዛ ውሃ ለመጨመር ታስቦ የሚደረግ መሰሪነት ከሆነ፥ ፈጽሞ የሚያመጣው አሉታዊ አንደምታ አይኖረውም፡፡ በአንፃሩ ግን፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕውነተኛና ቆራጥ ታጋይ ልጆቹንና እንደ ይሁዳ ጌታውን በሠላሳ ብር የሸጠውን ከሃዲ ለይቶ ለማወቅ የበለጠ ዕድል ይኖረዋል፡፡ ነገም እንደትላንትናው በወያኔ ፓርላማ ለመግባት ከአሁኑ መቋመጥ፥ መለስን ከመጥቀም አልፎ ተርፎ፥ ለሕዝቡም ይሁን ለሀገሪቱ የሚያስገኘው ዒምንት ጥቅም የለውም፡፡ የሕዝቡን ትግል በውርጭ ውሃ ለማደንዘዝ ወያኔንም የሕግ ማጠየቂያ እንዲያገኝ ለማድረግ ግን ጊዚያዊ አፍራሽ ሚና ሊጫወት ይችል ይሆናል፡፡ በወያኔ ፓርላማ እንግባ ብለው የሚወስኑ ክፍሎች ካሉ፥ ፀረ-ኢትዮጵያና ሕዝቧ ለሚሆኑት ፖሊሲዎችና ውሳኔዎች፥ የፓርላማ ድምፅ እየሰጡ ለመኖር ሲባል ሕዝብ እንደማይመርጣቸው ከአሁኑ በቅድሚያ ማወቅ አለባቸው፡፡ ይህንን የፖለቲካ ዘማዊነት አንግቦ መውተርተር፥ የግል ሰብዕናን ከማዋረድ አልፎ ተርፎ የኢትዮጵያንም ሕዝብ የአዕምሮ ብስለትና የሰብዕና ልዕልና እንደመፈታተንም ጭምር ይቆጠራል፡፡ በሚቀጥለው የወያኔ ፓርላማ ውድድር በርከት ብለን ብንገባ የወያኔን ልብና አዕምሮ ለመለወጥ እንችል ይሆናል የሚባለው ቧልትና ከንቱ የፖለቲካ ስሌት ደግሞ ያው ዞሮ ዞሮ በራስ ላይ እንደመቀለድና የሕዝቡንም የትግል ቱማታ ለማኮላሸት፥ አቅጣጫውንም ለማስቀየር መጣር ብቻ ሳይሆን፥ ብሔራዊ ክህደትም ጭምር ነው፡፡ "ሕገ መንግሥት" የተባለውም ሆነ ፍርድ ቤቶች፥ ዳኞቹም ይሁኑ አቃቤ ሕጎች፥ የምርጫው ቦርድ አባላቱም ሆኑ የተሰጣቸው መመሪያ ያው በጠቅላላው የወያኔን ጥቅም አስከባሪዎች በመሆናቸው በሚቀጥለው የምርጫ ውጤት ላይ አንዳችም ለውጥ አያመጣም፡፡ ወያኔ በሥልጣን ላይ እስካለ ደረስ ደግሞ እነኝህ ሁኔታዎች ተለውጠው የዴሞክራሲ አየር ይነፍሳል ተብሎ አይታሰብም፡፡ እንዲያው ዝም ብሎ መዳከር ነው፡፡ ማንኛውም ሰው፥ በአንድ ጊዜ ለሁለት ጌቶች በተመሳሳይ ታማኝነት ሊያገለግል አይችልም፡፡ ተቃዋሚ ኃይሎች የሚባሉትም የወያኔን ዓላማና ፖሊሲ እያራመዱ፥ ወዲያው ደግሞ ለሕዝብ እየታገልን ነው ማለት አይችሉም፡፡ አንድ ሰው፥ በአንድ ጊዜ ባንዳም አርበኛም ሊሆን ከቶ አይቻለውም፡፡ አንዱን ትቶ ሌላውን ለመምረጥ ግን የግል መብቱ ነው፡፡

የወያኔን ፓርላማ እንደ መታገያ መድረክ ለመጠቀም እንዲቻል መግባት ያስፈልጋል የሚባል አመለካከት ያላቸው ክፍሎች ሊገነዘቡት የሚገባው ነገር

ቢኖር፥ የወያኔ-ፓርላማ መድረክ የወያኔ እንጅ የኢትዮጵያ ሕዝብም ሆነ የተቃዋሚው ክፍል መድረክ አለመሆኑን ነው። ምንም ቁም ነገር ሊከናወንበት በማያስችል በወያኔ ፓርላማ ገብቶ መድረክ እናገኛለን ብሎ ማሰብ፥ አንድም፥ አሁንም ቢሆን የነመለስ ዜናዊን ማንነት በሚገባ አለመረዳት ይሆናል፥ ወይም ደግሞ፥ ነገሩ ሁሉ እማይሆን መሆኑን በመረዳት አይተነው ጊዜ ወደ አደላበት የሚል አቋም ለመውሰድ የታሰበ የተስፋ መቁረጥና የችንፈት ውሳኔ ነው። በሁለቱም በኩል የሚወሰዱት ውሳኔዎች በኃላፊነት ከማስጠየቅ አያድኑም። ከወያኔ ጋር በወንጀል አባሪ ተባባሪ መሆንንም ያሳያል እንጂ!

ደርግ ተወግዶ ወያኔ ከተተካበት ከዛሬ 17 ዓመታት ወዲህ በሀገራችን የሽግግር ወቀት የመንግሥትን ባኅርይና ተግባር አስመልክቶ አንዳችም የተለወጠ ነገር እንደሌለ የሚከራከር ዜጋ የለም፤ ኢትዮጵያ የምትገዛው በአምባገነን ቡድኖች ነው። በሕዝብና በዚህ የገዥ ቡድን መካከል ያለው ግንኙነት፥ በአጥፊና ጠፊ እንዳለው ዓይነት ነው። የወያኔ መሪዎች፥ ሀገር እያጠፉ፥ ሕዝብ እየጨረሱ፥ ኃብት እያሸሹ ሀገር እየሸጡ ቆይተዋል። በመጨረሻ ጊዜያቸውም የሚያደርጉት ያው ማንኛውም አምባገነን እንደሚያደርገው ይሆናል። አጥፍቶ መጥፋት፥ ወይም ሀገር አጥፎቶ መሸሽ ። በዚህ የመጨረሻ ጊዜ ውሳኔ አወሳሰድ ማንኛቸውም አምባገነኖች፥ ከሞላ ጎደል ይመሳሰላሉ። ሂትለር ጀርመንን አጥፍቶ እራሱን ገድሎ፥ እሬሳውን እንዲቃጠል አስደረገ። ሙሶሊኒ የኢትዮጵያን ሕዝብ ጨርሶ ኢጣሊያንን አጥፍቶ ሬሳው ተዘቅዝቆ ተሰቀለ። ኒኮላይ ቻውቸስኮ በሩማንያ ሕዝብ ከነባለቤቱ በአደባባይ በጥይት ተደበደበ። የዩጋንዳው ኢዲ አሚን ዳዳና የኢትዮጵያው መንግሥቱ ኃይለማርያም የሚገዙትን ሕዝብ እልፍ አዕላፍ ዜጋ ጨርሰው ሀብት ዘርፈው ፈርጥጠው ሄዱ። የወያኔ መሪዎችም ከዚህ ክስተት የተለየ ዕድል ሊያገኙ አይችሉም። ምክንያቱም፥በመጨረሻው ወቅት፥ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጣ ማንም ኃይል ሊያመልጥ ስለማይችል ነው።

ወያኔዎቹ፥ ከአለፈው የግንቦቱ ሕዝባዊ አመፅ ወዲህ የመውጫቸውን ስልትና አማራጭ በማሰናዳት ላይ እንደሚገኙ ግልፅ ሆኗል። ተባባሪዎቻቸውና ደጋፊዎቻቸው ዛሬ ኃብት በማሸሽ ላይ ናቸው። በአሁኑ ወቅት የትግራይ ተወላጆች በአውሮጳና በአሜሪካ በብዛት እየጎረፉ እንደሆነ የአደባባይ ምሥጢር ሆኗል። መለስና ጓደኞቹ የቆዩትን ያህል ቆይተው ሲሄዱ፥ ሀገሪቱ እንድትበጣበጥ ከማድረግ እንደማይመለሱ፥ ሳይታለም የተፈታ ነው። የተቃዋሚው ክፍል ይህንን አደጋ ለመከላከል ምን ያህል እንደሚያሳስበው የኢትዮጵያ ሕዝብ እርግጠኛ አይደለም።

በወቅቱ የኢትዮጵያ የፖለቲካ መልከዓ-ምድር፥ ሦስት የፖለቲካ ኃይሎች ተሰልፈዋል። በአንድ ጎራ ወያኔ ሲሆን፥ በሁለተኛ ደረጃ የትግሉ አቅጣጫ የጠፋባቸው ብሎም ምናልባት ለጥገናዊ ለውጥ ስንል ከወያኔ ጋር ደጅ እንጥና የሚሉ ሲሆኑ፥ በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ በዓላማቸው ፀንተው፥ በሀገራቸው ብሄራዊ ጥቅም ሳይደራደሩ ለሥርዓት ለውጥ የሚታገሉት ናቸው።

ፍጥጫው ወደየት ሊያመራ እንደሚችል ብዙ ምስጢር አይደለም። ምናልባትም የትግሉ ደረጃ እየከረረ፥ ፍጥጫው እየጦፈ፥ ሕዝባዊው አመፅ እየጠነከረ ሲመጣ፥ ዳግማዊ የካቲትን ደወል የሚደውል ወቅት ለመስማት እሩቅ አይሆንም። ይህንን አደገኛ ሁኔታን ለመቆጣጠር ካስፈለገ በግድ የሽግግር ወቅት ሊፈጠር ይገባል የሚል አማራጭም ማቅረብ፥ ከአጥፊና ጠፊ ሁኔታ ለመዳን ይቻላል ብሎ ኢሕአፓ ከልብ ያምንበታል። ይህም ሀገሪቱን ከሚቃጣባት አደጋ ለመከላከል ያስችላል ከሚል ኃላፊነት ነው። ከዚህም በተያያዘ ደግሞ ለዚህ ወቅት መሳሪያና መድኅን ብሎም ለሀገሪቱ የሚበጅ ሰላምና መረጋጋት ሊያሰፍን ይችላል ተብሎ የተገመተው፥ የብሔራዊ አንድነት መንግሥት መመሥረት መሆኑን በርካታ የሀገሪቱ የፖለቲካ ተንታኞች ይቀበሉታል። በሀገሪቱ ብሔራዊ ዕርቅ ለማምጣትም ዓይነተኛ ሚና ይጫወታል። ወያኔዎቹ ግን ይህንን አውደ ኃሳብ አይቀበሉትም። "ማን ተጣላና ነው ዕርቅ ዕርቅ የምትሉት" እያሉ ያላግጣሉ። በዚህ በሽግግር ወቅት በሚመሰረተው የብሔራዊ አንድነት መንግሥት ውስጥ ሁሉም የፖሊቲካ ድርጅት መካተት አስፈላጊና መሠረታዊ እንደሆነ መታወቅ ይኖርበታልም ተብሏል። ከሽግግር ወቅት ወደ ቋሚና በምርጫ ወደሚሰየም መንግሥት ለመሸጋገር፤ ከወዲሁ፥ ዛሬ መሠረታዊ የሆነ ተግባራትን ማከናወን ይጠይቃል። ጥልቅና ውስብስብ ችግሮች ያሉባትን ሀገር አሁን ከወደቀችበት ማጥ ለማውጣትና በኀልውናዋ የተቃጣባትን አደጋ ለመከላከል፥ መለስን ብቻ በመጣል ዘረኛ አገዛዙን ጠጋግነን እንቀጥል የሚባለው ጥድፊያ የትም እንደማያደርስ መታወቅ አለበት። የወያኔ ርዝራዦችና ባንዳ ከኻድያን በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘላቂ ጥቅም ላይ የሚያደርጉትን ደባ የኢትዮጵያ ሕዝብ እየተከታተለ እንደሚያከሽፈው ማንም ሊጠራጠር አይችልም። ባንዶቹ የሚመሳጠሩበት እኩይ ተግባር ፋይዳ አያመጣም። በመሆኑም ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁኔታውን ከሁሉም አንፃር ተመልክቶ፥ ወዳጅ ጠላቱን እየለየ ትግሉን እንዲያፋፍም ጥሪያችንን እናስተላልፋለን። የነገው ወሳኝ ድል የዛሬን ቆራጥ ትግል ይጠይቃልና!